# በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር

የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት
Ethiopian Metrology Institute

# የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት

# የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ

## የተከለሰ

ጥር 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## ይዘት

1. መግቢያ ........ 1
1.1 የኢትየጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት ገጽታ ........ 1
1.1.1 አመሰራረት ........ 1
1.2 የተቋሙ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ እሴቶች፣ ሥልጣንና ተግባር ........ 2
1.2.1 ተልዕኮ ........ 2
1.2.2 ራዕይ ........ 2
1.2.3 ዕሴቶች ........ 2
1.2.4 በእቅድ ዘመኑ የኢንስቲትዩቱ ዋና ዋና ዓላማዎች፣ ........ 2
1.2.5 የኢንስቲትዩቱ ግቦች ........ 3
2. የልማት ዕቅዱ አንድምታዎች እና የሚጠበቁ ውጤቶች ........ 3
2.1 የዓበይት ተግባራት ግቦች እና ዋና ዋና ተግባራት ........ 3
3. የ2015 በጀት ዓመት ዒላማዎችና የድርጊት መርሃ ግብር ........ 10
4. የዓመቱን ዕቅድ ለማሳካት የሚተገበሩ ማስፈጸሚያዎች ........ 20
4.1 የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች ........ 20
4.2 ተቋማዊ የትራንስፎርሜሽን እና የኢኮቴ ዲጂታላይዜሽን አጀንዳዎች ........ 20
4.3 የክትትልና ግምገማ ስርዓት ........ 21
4.3.1 ሪፖርት ........ 21
4.3.2 የአካል ግምገማ ........ 21
4.3.3 ሱፐርቪዥን ........ 22
5. ዕቅዱን ለማሳካት በየምዕራፍ የሚሰሩ ስራዎች ........ 22
5.1 የዝግጅት ምዕራፍ (ሐምሌ-ነሀሴ) ........ 22
5.2 የተግባር ምዕራፍ (መስከረም-ግንቦት 20) ........ 22
5.3 የማጠቃለያ ምዕራፍ (ግንቦት 21 -ሰኔ 30 ........ 22
6. የ2015 በጀት ዓመት የሰው ሃይል ፍላጎት ........ 23
7. 2015 በጀት ዓመት የፊዚካል እና የፋይናንስ ዕቅድ በየውጤቱ (የጸደቀ በጀት) ........ 25

## 1. መግቢያ

ሀገራችን ኢትዮጵያን በ2022 ዓ.ም የአፍሪካ የብልጽግና ተምሳሌት ለማድረግ ሀገራዊ ራዕይ ተሰንቋል፡፡ በዚህ ረገድ የተለያዩ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ተቀርፀዉ በየዘርፉ ለተግባራዊነታቸው ከፍተኛ ርብርብ እና ጥረት እየተደረገ ይገኛል፡፡ ይህንን የልማት ጉዞ በስኬት ለማጠናቀቅ የሚያስችሉና ለዕድገት አመቺ የሆኑ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ የተደረገ ሲሆን ዕቅዱን ከማሳካት አኳያ ከፍተኛ ኃላፊነት ከተጣለባቸው የኢኮኖሚያዊ ልማት ዘርፎች መካከል በዋናነት የኢንዱስትሪ ልማትና ንግድ ዘርፍ አንዱ ነው፡፡

ምርቶችና አገልግሎቶች በዓለም አቀፍ ገበያ ላይ በጥራትና በምርታማነት ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ለማስቻል በተዘረጋው የጥራት መሰረተ ልማት መዋቅር ውስጥ የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት በዘርፉ ምርምር በማካሄድ፣ ለኢንዱስትሪዎችንና ለአገልግሎት ሰጪ ተቋማት የካሊብሬሽን፣ የስልጠናና ምክር አገልግሎት በመስጠት፣ ፍላጎቶቻቸውንና ችግሮቻቸውን በመረዳት አዳዲስ የአለካክ መስኮች በመክፈት እና የሌሎች አገሮች የተሻለ አሰራሮችን ልምዶችን በመቅሰም አስፈላጊውን ሚና ይጫወታል፡፡

በሌላ በኩል የከፍተኛ ትምህርት፣ የምርምር፣ የፍተሻ፣ የጤናና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚሰጧቸው አገልግሎቶች ውጤታማ እንዲሆኑ ለማድረግ በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ ምርምር በማካሄድ፣ የመጠቀም አቅም የመገንባት፣ ዘመናዊ የሆነ የሳይንስ መሳሪያዎች የማስተዳደር ስርዓት የመዘርጋት እና የቴክኒክ አገልግሎቶችን (ስልጠና፣ ምክር፣ መረጃ፣ ጥገናና ተዛማጅ ተግባራቶች) የመስጠት ኃላፊነቱን በመወጣት ላይ ይገኛል፡፡

### 1.1 የኢትየጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት ገጽታ

#### 1.1.1 አመሰራረት

በ2001 ዓ.ም በመንግስት በጸደቀው የጥራት መሰረተ-መዋቅር ስትራቴጂ መሰረት የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት እንዲቋቋም በቀረበው የውሳኔ ሃሳብ የካቲት 3 ቀን 2003 ዓ.ም በሚኒስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 194/2003 ብሄራዊ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩቱ ተቋቁሟል፡፡

በዚህም መሰረት በተለያዩ ተቋማት ይሰሩ የነበሩ ስራዎች ማለትም ከቀድሞው የኢትዮጵያ የጥራትና የደረጃዎች ባለስልጣን የሥነ-ልክ ስራዎችን ፤ ከኢትዮጵያ የጨረራ መከላከያ ባለስልጣን የጨረራ ልኬቶች ትስስር የመጠበቅ ስራ እና የጨረራ ልኬትና ካሊብሬሽን አገልግሎት ስራ እንዲሁም በኢትዮጵያ የሳይንስ መሳሪያዎች ማዕከል ይሰሩ የነበሩትን ተግባራት ሙሉ በሙሉ (የሳይንስ መሳሪያዎች ጥገና፣ ስልጠና፣ የምክርና መረጃ አገልግሎቶች) ከተጠቀሱት ተግባራት ጋር ተስተጋብረው በኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት ዓላማ ፣ስልጣንና ተግባር ተካተዋል፡፡

## 1.2 የተቋሙ ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ እሴቶች፣ ሥልጣንና ተግባር

### 1.2.1 ተልዕኮ

በሥነ-ልክ እና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፎች የጎለበተ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት፣ ችግር ፈቺ ምርምሮችን በማከናወን፣ ቀጣይነት ያለው አቅም በመገንባትና የቴክኖሎጂ ሽግግር በማምጣት ለደንበኞቻችን ብቃት ያለው አገልግሎት በመስጠት የምርትና የአገልግሎት ጥራትና ውጤታማነትን እና በሳይንስ መሣሪያዎች ዘርፍ በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው በአፍሪካ ተመራጭ የሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት መሆን

### 1.2.2 ራዕይ

በ2022 ዓ.ም በሥነ-ልክ እና በሳይንስ መሣሪያዎች ዘርፍ በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያለው በአፍሪካ ተመራጭ የሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት መሆን

### 1.2.3 ዕሴቶች

- ሳይንሳዊ አሰራርን ማስረጽ፤
- ሙያዊ ብቃትና ስነምግባር፤
- ቀጣይነት ያለው መሻሻል፤
- በጎ ህሊናና ቅን ልቦና፤
- ምላሽ ሰጪነት፤
- የዓላማ ፅናት፤
- ሚዛናዊነት፤
- ስትራቴጂካዊ አጋርነት ናቸው፡፡

### 1.2.4 በዕቅድ ዘመኑ የኢንስቲትዩቱ ዋና ዋና ዓላማዎች፣

- ከዓለም ዓቀፍ ሥነ-ልክ ስርዓት ጋር የተጣጣመ ብሔራዊ የስነ-ልክ ስርዓትን የመዘርጋትና በዘርፉ የቴክኖሎጂ ሽግግርን የማምጣት፤
- የአገሪቱን ብሔራዊ የመለኪያ ኢታሎኖችና የተመሰከረላቸውን የማመሳከሪያ ስረቶች ከዓለም ዓቀፍ የመለኪያ ኢታሎኖች ጋር ለማመሳከር፤ለመጠበቅና ለማሰራጨት፤ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት የመዘርጋትና የመተግበር፤
- በሥነ-ልክ እና በሳይንስ መሳርያዎች ዘርፍ ጥናት እና ምርምሮችን የማከናወንና የመደገፍ፤
- የሳይንስ መሳሪዎችን ጥገና ብሔራዊ አቅም መገንባትና የጥገና አገልግሎት መስጠት፤
- ለሳይንስ መሳሪያዎች ተጠቃሚዎች የቴክኒክ፣ የስልጠናና የምክር የመረጃ አገልግሎቶችን በመስጠት ተግባሮቻቸውን በብቃት እንዲያከናውኑ መደገፍ፤

### 1.2.5 የኢንስቲትዩቱ ግቦች

ግብ 1. የደንበኛ /የባለድርሻ እርካታ ማሳደግ
ግብ 2. ተደራሽነትን ማሳደግ
ግብ 3 የበጀት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ
ግብ 4 የፋይናንስ ምንጮችን ማበራከት
ግብ 5 አለም አቀፍ ተቀባይነት ማሳደግ
ግብ 6 የአለካክ ወሰኖችን ማሳደግ
ግብ 7 አሰራር ቅልጥፍናን ማሻሻል
ግብ 8 ቅንጅታዊ አሰራር ማሻሻል
ግብ 9 የሰራተኛውን ብቃት ማሳደግ
ግብ 10. የስራ አካባቢና መሰረተ ልማት ማሻሻል
ግብ 11 የክትትልና የግምገማ ስርዓትን ማሻሻል

የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ በሶስት ትኩረት መስኮች (ጥናትና ምርምር ፣ የላቀ አገልግሎት፣ የአሰራር ስርዓትና የአቅም ግንባታ) እና በ11 ስትራጂያዊ ግቦች ተለይቶ ታቅዷል፡፡ በመሆኑም በተገነባው ጠንካራና ቀጣይነት ያለው የኢንስቲትዩቱን የለውጥ ሠራዊት ከዓለም ዓቀፍ ስነ-ልክ ስርዓት ጋር የተጣጣመ ብሄራዊ የሥነ-ልክ ስርዓትና ብሔራዊ የሳይንስ መሳሪያዎች አቅም ግንባታን ለማጠናከርና ተግባራዊ ለማድረግ በ2015 በጀት ዓመት የመጀመሪያውን የስድስት ወራት የዕቅድ አፈጻጸም በመገምገም ዕቅዳችንን የከለሰን በመሆኑ ተግባራዊ ለማድረግ  ከፍተኛ ርብርብ የሚደረግ ይሆናል፡፡

## 2. የልማት ዕቅዱ አንድምታዎች እና የሚጠበቁ ውጤቶች

የኢትዮጵያ ሥነ-ልክ ኢንስቲትዩት የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ ሲዘጋጅ የውጤት ተኮር ሥርዓት (BSC) አግባብ የተከተለ ሲሆን ይህም ተቋሙ የተሰጠውን ተልዕኮ እንዲፈፅምና ተልዕኮው መሳካቱን እንዲያረጋግጥ የሚያግዝ ነው፡፡ ዕቅዱም ሲዘጋጅ መሰረት ያደረገው የኢንስቲትዩቱን የ10 ዓመት መሪ ዕቅድ እና ስትራቴጂክ ዕቅድ (2013-2017) መሰረት በማድረግ ፣ የ2015 በጀት ዓመት የመጀመሪያውን ስድስት ወራት የዕቅድ አፈጻጸም በመገምገም  እና የኢንስቲትዩቱን ጥንካሬ፣ ድክመት፣ መልካም አጋጣሚ እና ስጋትን በመተንተን የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ ተከልሶ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ የ2015 በጀት ዓመት የተከለሰው ዕቅድ ሶስት ስትራቴጂያዊ የትኩረት መስኮች ያሉት ሲሆን በአራቱ የአፈጻጸም ዕይታዎች መሰረት 11 ስትራቴጂዊ ግቦችን ያካተተ ነው፡፡ በግቦቹም ስር ዋና ዋና እና ዝርዝር ተግባራትን አካቶ ይዟል፡፡

### 2.1 የዓበይት ተግባራት ግቦች እና ዋና ዋና ተግባራት

**የተገልጋይ እይታ 40%**
**ግብ 1. የደንበኛ /የባለድርሻ እርካታ ማሳደግ**
**1.1 ጥናትና ምርምር ማካሄድ**
1.1.1 4 ጥናትና ምርምር ማካሄድ

**1.2 የካሊብሬሽን አገልግሎቶች መስጠት**

1.2.1 31065 የካሊብሬሽን አገልግሎቶች መስጠት

**1.3 የጥገና አገልግሎቶች መስጠት**

1.3.1 ለ300 የሳይንስ መሳሪያዎች የጥገና አገልግሎት መስጠት

**1.4 የስልጠና አገልግሎቶች መስጠት**

1.4.1 በሥነ-ልክ ዘርፍ እና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ 4 ጊዜ በድምሩ 8 ጊዜ ሙያዊ ስልጠና መስጠት

**1.5 የምክር አገልግሎቶች መስጠት**

1.5.1 በሥነ-ልክ ዘርፍ እና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ የሚቀርቡ የአገልግሎት ጥያቄዎች 100% የምክር አገልግሎቶች መስጠት

**1.6 የብቃት ማረጋገጥ አገልግሎቶች መስጠት**

1.6.1 ለ26 የህክምና መሳሪያዎች ተከላ፣ ጥገናና ኮሚሽኒንግ የብቃት ማረጋገጥ አገልግሎቶች መስጠት

**1.7 የተጠቃሚ እርካታ መመዘን**

1.7.1 የተጠቃሚ እርካታ ጥናት ማድረግ

**ግብ 2. ተደራሽነትን ማሳደግ**

**2.1 በተንቀሳቃሽ ላብራቶሪ አዳዲስ አገልግሎት መስጠት**

2.1.1 በተንቀሳቃሽ ላብራቶሪ በኤሌክትሪካል አለካክ መስክ የካሊብሬሽን አገልግሎት መጀመር

**2.2 በቅርንጫፍ ካሊብሬሽን ላብራቶሪዎች የአገልግሎት ወሰን ማስፋት**

2.2.1 በቅርንጫፍ ካሊብሬሽን ላብራቶሪዎች በሙቀት አለካክ (thermometers, moisture) መስክ ካሊብሬሽን መጀመር

**2.3 የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት**

2.3.1 የጥገና ወርክሾፕ እና የካሊብሬሽን ላቦራቶር ለማቋቋም ጥያቄ ለሚያቀርቡ የግል ባለሃብት፣ አምራችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት 100 % የቴክኒክ ድጋፍ አገልግሎት መስጠት

**2.4 የኢንስቲትዩቱን ዌብሳይት ለጎብኚዎች ምቹ እንዲሆን ማድረግ**

2.4.1 ኢንስቲትዩቱን በሚመለከት 12 ለድረ-ገጽ የሚመጥኑ መረጃዎችን ማዘጋጀትና መጫን

**2.5 የግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠት**

2.5.1 በተመረጡ 3 አካባቢዎች እና በዩኒቨርስቲዎች የግንዛቤማስጨበጫ መስጠት

**የፋይናንስ እይታ 10%**

**ግብ 3 የበጀት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ**

**3.1 የበጀት አጠቃቀምን መከታተል**

3.1.1 የፀደቀውን በጀት በዕቅዱ መሰረት 100% መጠቀም

**3.2 የአገልግሎት ክፍያዎችና ተሰብሳቢ ሂሳቦች በወቅቱ ለመንግስት ገቢ ማድረግ**

3.2.1 12 ሚሊዮን ብር የአገልግሎት ክፍያዎችና ሌሎች ገቢዎችን በማስገባት በወቅቱ ለመንግስት ገቢ ማድረግ

**3.3 የፋይናንስ ኦዲት ማከናወንና መከታተል**

3.3.1 አምስት (5) የሂሣብ ኦዲት ሪፖርት እና 1 ክዋኔ ኦዲት ማዘጋጀት

**ግብ 4 የፋይናንስ ምንጮችን ማበራከት**

**4.1 ፕሮጀክቶች በማዘጋጀት ድጋፍ መጠየቅ**

1 ፕሮጀክቶች በማዘጋጀት ድጋፍ ማፈላለግ

**የውስጥ አሰራር 25%**

**ግብ 5 አለም አቀፍ ተቀባይነት ማሳደግ 40%**

**5.1 ዓለም ዓቀፍ እርከን ተዋረድ ትስስር መጠበቅና ማሰራጨት**

5.1.1 በ4 (በዳይሜንሽናል፣ በግዝፈት፣ በኤሌክትሪካልና በግፊት) የአለካክ መስኮች የመጀመርያ ደረጃ የአለካክ መስኮች ዓለም ዓቀፍ እርከን ተዋረድ ትስስር መጠበቅ

**5.1.2 211** ሁለተኛ ምድብ ማነጻጸሪያ መለኪያ መሳሪያዎች ዓለም አቀፍ የዕርከን ተዋረድ ትስስር ማሰራጨት

### 5.2 ዓለም አቀፍ እውቅና የተገኘባቸው የአለካክ መስኮች/ወሰን ማስቀጠል

5.2.1 (በግዝፈት፣ በኤሌክትሪካል፣ በሙቀት፣ በይዘት እና ሚዛን) ዓለም አቀፍ እውቅና የተገኘባቸው የአለካክ መስኮች ማስቀጠል

5.2.2 ዕዉቅና ባልተገኘባቸው 6 የአለካክ መስኮች (በዳይሜንሽናል፣ በሀይል፣ ይዘት (ላርጅ ቮልዩም) ፣ በቶርክ፣ በሀርድነስ፣ በጊዜና ድግግሞሽ) የአለካክ መስኮች በተዘጋጀው ፕሮግራም መሰረት ዓመታዊ የውስጥ የጥራት ኦዲት በማከናወን የእርምት እርምጃ መውሰድ

5.2.3 በ3 አዳዲስ የንጽጽር ፕሮግራሞችን በግዝፈት፣ በግፊት እና በሚዛን የአለካክ መስኮች ማፈላለግ እና ማካሄድ

### 5.3 በአዳዲስ የአለካክ መስኮች/ወሰን እውቅናን ማስፋት

5.3.1 በ2 የአለካክ መስኮች በወበቅ (Humidity) እና በእርጥበት (Mositure) መስክ የካሊብሬሽን የአሰራር ስርዓት ሰነድ ማዘጋጀት እና ዕውቅና ማስፋት

### 5.4 በ3 አለካክ መስኮች በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት (BIPM-KCDB)ማስመዝገብ

5.4.1 ኤሌክትሪካል፣ ሙቀት እና ይዘት የአለካክ መስኮችን በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት /BIPM-KCDB/ የካሊብሬሽን ልኬት ብቃት/CMC/ ለማስመዝገብ የጥራት ሥራ አመራር አሰራር ሥርዓት ሰነድ በክፍለ አህጉራዊ የሥነ-ልክ ድርጅት የጥራት ቴክኒካል ኮሚቴ /AFRIMETS TC-QS/ ማስገምገም

### 5.5 በአህጉራዊና ዓለምአቀፍ የሥነልክ ተቋማት በመሳተፍ ስትራቴጂያዊ ተጠቃሚነትን ማሳደግ

5.5.1 ከዓለምአቀፍ (BIPM) ከአህጉራዊ AFRIMET እና NEWMET ዓመታዊ ስብሰባ ላይ አገሪቷን ወክሎ መሳተፍ

5.5.2 ከአህጉራዊ AFRIMET እና NEWMET  ዓመታዊ የቴክኒካል ስብሰባዎች ላይ መሳተፍ እና የንጽጽር ፕሮግራሞችን ማመቻቸት

### 5.6 የጥራት ስራ አመራር ስርዓቶችን በመለየት ተግባራዊ ማድረግ

5.6.1 በ 4 የስራ ሂደቶች (በሳ/መ/ስ/ም/ዳ/ት፣ በሳ/መ/ቴ/ም/ዳ/ት ፣በፋይናንስ ዳ/ት ፣ሰው ኃብት አስ. ዳ/ት (ISO 9001:2015) ተግባራዊ ማድረግ

**ግብ 6 የአለካክ ወሰኖችን ማሳደግ**

6.1 የአለካክ መስክ/ወሰን ማሳደግ

6.1.1 አራት (4) የአለካክ መስኮች/ወሰኖች ማሳደግ

**ግብ 7 አሰራር ቅልጥፍናን ማሻሻል**

**7.1 የተሻሻሉና አዳዲስ ኦላይን ሲስተሞች ተግባራዊ ማድረግ**

**7.1.1** በተቋሙ ጥቅም ላይ እየዋሉ ያሉትን ሲስተሞችን (IFMIS, ICMIS፣EGPS) አጠናክሮ ለማስቀጠል ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ

7.1.2 የካሊብሬሽን እና የጥገና አልግሎት (አውቶሜት) E- service ኦላይን በማድረግ የአገልግሎት አሰጣጡን ማዘመን

**7.2 ደንቦች፣ መመሪያዎችና ውሎች ማዘጋጀትና መከለስ**

7.2.1 የአገልግሎት ክፍያ የዋጋ ተመን ሰነድ መከለስ እና ለገ/ሚ ማቅረብ

7.2.2 የሚጸድቁ ረቂቅ የህግ ማእቀፎችን ሂደት መከታተል

**7.3 የጥናት ምርምር እና መመሪያ ማዘጋጀት**

7.3.1 የጥናት እና ምርምር መመሪያ ማጸደቅ ተግባራዊ ማድረግ

**7.4 የአገልግሎት ፣የመሳሪያ ግዢ እና የአባልነት ክፍያ መፈጸም**

7.4.1 በግዥ ዕቅዱ መሠረት የሀገር ውስጥ እና የውጪ ግዥ በመፈፀም ማጠናቀቅ

**7.5 የንብረት ቆጠራ ማካሄድ እና ስራ ላይ የማይውሉ ንብረቶችን በወቅቱ ማስወገድ**

**7.5.1** በዓመታዊ ንብረት ቆጠራ ውጤት መሠረት ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ንብረቶችን በየዓይነታቸው መለየት እና በአስወጋጅ ኮሚቴ እንዲወገዱ ማድረግ

**ግብ 8 ቅንጅታዊ አሰራር ማሻሻል**

**8.1 ከከፍተኛ ትምህርትና የምርምር ተቋማት ጋር በትብብር መስራት**

8.1.1 ከተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች ለሚመጡ 21 ተማሪዎች ኢንተርንሺፕ ፕሮግራም ማካሄድ

**8.2 ከአቻ የውጪ የሥነ-ልክ ተቋማት ጋር በትብብር መስራት**

8.2.1 ከ5 ከአቻ የውጪ የሥነ-ልክ ተቋማት ጋር የተፈረመውን ስምምነት ማደስ እና ተግባራዊነቱን መከታተል

**8.3 ከጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ጋር በትብብር መስራት**

8.3.1 ከጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ጋር በትብብር መስራት

**መማማርና እድገት 25%**

**ግብ 9 የሰራተኛውን ብቃት ማሳደግ**

**9.1** የሰው ሀብት ልማት ማልማት

9.1.1 ለ180 ሠራተኞች ስልጠና መስጠት

9.1.2 ለ3 ሰራተኞች ሁለተኛ እና ሶስተኛ ዲግሪ የትምህርት ዕድል መስጠት

9.2 **የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ ስልቶችን መቀየስ፣፣ መከታተልና ማጠናከር**

9.2.1 ኤች አይቪ በደማቸዉ ዉስጥ ለሚገኝ ሁለት የኢንስቲትዩቱ ሠራተኞችና ወላጆቻቸዉን ላጡ ሁለት ሕፃናት ድጋፍ ማድረግ

9.2.2 ዝቅተኛ የደሞዝ ተከፋይ የሆኑ ሴቶችና ወጣት ሠራተኞችን ፕሮጀክት በመንደፍ ገቢያቸዉን እንዲያሳድጉ ማመቻቸት

**9.3 የተቀናጀ የሙስናና የመከላከል ስትራቴጂ ተግባራዊ ማድረግ**

9.3.1 በተቋም የሚገኙ የስራ ክፍሎችን የሙስና ተጋላጭነት ስጋት መለየት፣ ደረጃ መስጠት

9.3.2 የኢንስቲትዩቱን የሥነ-ምግባር ደንብ ማዘጋጀት

**ግብ 10. የስራ አካባቢና መሰረተ ልማት ማሻሻል**

**10.1 የአካባቢ ብክለትንና በህብረተሰቡ ጤና ጉዳት መቀነስ**

10.1.1 የሁለተኛ ምድብ የጨረራ ላቦራቶር /SSDL/ የ X-ray machine እና የ Cs-137 Gamma source shutter ብልሽት ተከታትሎ በማስጠገን እንደገና አገልግሎት ማስጀመር

**10.2 ተስማሚ የሆኑ የሥራ ቦታዎች ማዘጋጀት**

10.2.1 ተስማሚ የሆኑ የሥራ ቦታዎች ማዘጋጀት (ግቢ ውበት፣ፋሲሊቲ ፣ እድሳት እና የሰራተኛ መመገቢያ)

**10.3 የሰው ኃይል ማሟላት**

10.3.1 በፀደቀው መዋቅር መሰረት ድልድል ማካሄድ

**10.4 የኢ/ኮ/ቴ መሠረተ ልማት ደህንነትና ወቅታዊነት ማስጠበቅ**

10.4.1 በተቋሙ የሚገኙ መሠረተ ልማቶችን (ሀርድዌር እና ሶፍት ዌር) አቅም መጨመር

**10.5 የለውጥና መልካም አስተዳደር የአሰራር ስርዓቶች መዘርጋት**

10.5.1 በዜጎች ቻርተር መሠረት አገልግሎት መሰጠቱን የትንተና ሰነድ ማዘጋጀት

**ግብ 11 የክትትልና የግምገማ ስርዓትን ማሻሻል**

**11.1** ፕሮጀክቶችን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ

11.1.1 ፕሮጀክቶችን በየሩብ በዓመቱ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ

**11.2 የውጤት ተኮር ዕቅድ ማዘጋጀትና አፈጻጸም መገምገም**

11.2.1 የውጤት ተኮር ዕቅድ ማዘጋጀት፣ በየደረጃው መፈራረም ፣ በየወሩ አፈጻጸም መገምገም እና ምዘና ማካሄድ

## 3. የ2015 በጀት ዓመት ዒላማዎችና የድርጊት መርሃ ግብር የተከለሰ

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | የ2014 አፈፃፀም (መነሻ) | የ2015 ግብ (ዓመታዊ) | ሩብ ዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| 1 | **የደንበኛ /የባለድርሻ እርካታ ማሳደግ ( ክብደት = 26.5 )** | | | | | | | | |
| 1.1 | **ጥናትና ምርምር ማካሄድ ( ክብደት = 4.5 )** | | | | | | | | |
| 1.1.1 | 4 ጥናትና ምርምር ማካሄድ | 4.5 | በቁጥር | 0 | 4 | | | 1 | 3 |
| 1.2 | **የካሊብሬሽን አገልግሎቶች መስጠት ( ክብደት = 7 )** | | | | | | | | |
| 1.2.1 | 31065 የካሊብሬሽን አገልግሎቶች መስጠት | 7 | በቁጥር | 25226 | 31065 | 5743 | 12294 | 21801 | 31065 |
| 1.3 | **የጥገና አገልግሎቶች መስጠት ( ክብደት = 4.5 )** | | | | | | | | |
| 1.3.1 | ለ300 የሳይንስ መሳሪያዎች የጥገና አገልግሎት መስጠት | 4.5 | በቁጥር | 279 | 300 | 25 | 115 | 205 | 300 |
| 1.4 | **የስልጠና አገልግሎቶች መስጠት ( ክብደት = 4.5 )** | | | | | | | | |
| 1.4.1 | በሥነ-ልክ ዘርፍ እና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ ሙያዊ ስልጠና መስጠት | 4.5 | በቁጥር | 0 | 2 | 2 | 4 | 6 | 8 |
| 1.5 | **የምክር አገልግሎቶች መስጠት ( ክብደት = 3.5 )** | | | | | | | | |
| 1.5.1 | በሥነ-ልክ ዘርፍ እና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ የሚቀርቡ የአገልግሎት ጥያቄዎች 100% የምክር አገልግሎቶች መስጠት | 3.5 | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 1.6 | **የብቃት ማረጋገጥ አገልግሎቶች መስጠት ( ክብደት = 1.5 )** | | | | | | | | |
| 1.6.1 | ለ26 የህክምና መሳሪያዎች ተከላ፣ ጥገናና ኮሚሽኒንግ የብቃት ማረጋገጥ አገልግሎቶች መስጠት | 1.5 | በቁጥር | 11 | 26 | 5 | 12 | 20 | 26 |
| 1.7 | **የተጠቃሚ እርካታ መመዘን ( ክብደት = 1 )** | | | | | | | | |
| 1.7.1 | የተጠቃሚ እርካታ ጥናት ማድረግ | 1 | በቁጥር | 1 | 1 | | | 1 | |

3. የ2015 በጀት ዓመት ዒላማዎችና የድርጊት መርሃ ግብር የተከለሰ

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደ ት | መለኪያ | የ2014 አፈፃፀ ም (መነሻ) | የ2015 ግብ (ዓመታ ዊ) | ሩብ ዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| 2 | **ተደራሽነትን ማሳደግ ( ክብደት = 13.5** | | | | | | | | |
| 2.1 | በተንቀሳቃሽ ላብራቶሪ አዳዲስ አገልግሎት መስጠት ( **ክብደት** = 3) | | | | | | | | |
| 2.1.1 | በተንቀሳቃሽ ላብራቶሪ በኤሌክትሪካል አለካክ መስክ የካሊብሬሽን አገልግሎት መጀመር | 3 | በቁጥር | 0 | 1 | 1 | | | |
| 2.2 | **በቅርንጫፍ ካሊብሬሽን ላብራቶሪዎች የአገልግሎት ወሰን ማስፋት ( ክብደት = 4)** | | | | | | | | |
| 2.2.1 | በቅርንጫፍ ካሊብሬሽን ላብራቶሪዎች በሙቀት አለካክ (thermometers, moisture) መስክ ካሊብሬሽን መጀመር | 4 | በቁጥር | 0 | 2 | 1 | 2 | | |
| 2.3 | **የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት ( ክብደት = 3)** | | | | | | | | |
| 2.3.1 | የጥገና ወርክሾፕ እና የካሊብሬሽን ላቦራቶር ለማቋቋም ጥያቄ ለሚያቀርቡ የግል ባለሃብት፣ አምራችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የቴክኒክ ድጋፍ አገልግሎት መስጠት | 3 | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 2.4 | **የኢንስቲትዩቱን ዌብሳይት ለጎብኚዎች ምቹ እንዲሆን ማድረግ ( ክብደት = 1)** | | | | | | | | |
| 2.4.1 | ኢንስቲትዩቱን በሚመለከት 12 ለድረ-ገጽ የሚመጥኑ መረጃዎችን ማዘጋጀትና መጫን | 1 | በቁጥር | 4 | 12 | 3 | 6 | 9 | 12 |
| 2.5 | **የግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠት ( ክብደት = 2.5)** | | | | | | | | |
| 2.5.1 | በተመረጡ 3 አካባቢዎች እና በዩኒቨርስቲዎች የግንዛቤማስጨበጫ መስጠት | 2.5 | በቁጥር | 2 | 3 | | 1 | 2 | 3 |
| 3 | **የበጀት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሳደግ ( ክብደት = 9)** | | | | | | | | |
| 3.1 | የበጀት አጠቃቀምን መከታተል ( **ክብደት = 4.5**) | | | | | | | | |
| 3.1.1 | የፀደቀውን በጀት በእቅዱ መሰረት 100% መጠቀም | 3 | በመቶኛ | 86 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |

3. የ2015 በጀት ዓመት ዒላማዎችና የድርጊት መርሃ ግብር የተከለሰ

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | የ2014 አፈፃፀም (መነሻ) | የ2015 ግብ (ዓመታዊ) | ሩብ ዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| 3.2 | **የአገልግሎት ክፍያዎችና ተሰብሳቢ ሂሳቦች በወቅቱ ለመንግስት ገቢ ማድረግ ( ክብደት = 1.5 )** | | | | | | | | |
| 3.2.1 | 12 ሚሊዮን ብር የአገልግሎት ክፍያዎችና ሌሎች ገቢዎችን በማስገባት በወቅቱ ለመንግስት ገቢ ማድረግ | 1.5 | በቁጥር | 11 ሚሊዮን | 12 ሚሊዮን | 1950000 | 4950000 | 8550000 | 1200000 |
| 3.3 | **የፋይናንስ ኦዲት ማከናወንና መከታተል ( ክብደት = 3 )** | | | | | | | | |
| 3.3.1 | አምስት(5) የሂሣብ ኦዲት ሪፖርት እና 1 ክዋኔ ኦዲት ማዘጋጀት | 3 | በቁጥር | 2 | 5 | 2 | 3 | 4 | 5 |
| 4 | **የፋይናንስ ምንጮችን ማበራከት ( ክብደት = 1 )** | | | | | | | | |
| 4.1 | **ፕሮጀክቶች በማዘጋጀት ድጋፍ መጠየቅ ( ክብደት = 1 )** | | | | | | | | |
| 4.1.1 | 1 ፕሮጀክቶች በማዘጋጀት ድጋፍ ማፈላለግ | 1 | በቁጥር | 1 | 1 | | | | 1 |
| 5 | **አለም አቀፍ ተቀባይነት ማሳደግ ( ክብደት = 10.07 )** | | | | | | | | |
| 5.1 | **ዓለም ዓቀፍ እርከን ተዋረድ ትስስር መጠበቅና ማሰራጨት( ክብደት = 1.5 )** | | | | | | | | |
| 5.1.1 | በ4 (በዳይሜንሽናል፣ በግዝፈት፣ በኤሌክትሪካልና በግፊት) የአለካክ መስኮች የመጀመርያ ደረጃ የአለካክ መስኮች ዓለም ዓቀፍ እርከን ተዋረድ ትስስር መጠበቅ | 1.5 | በቁጥር | 3 | 4 | | | 2 | 4 |
| 5.1.2 | 211 ሁለተኛ ምድብ ማነጻጸሪያ መለኪያ መሳሪያዎች ዓለም አቀፍ የዕርከን ተዋረድ ትስስር ማሰራጨት | 1 | በቁጥር | 195 | 211 | 39 | 101 | 165 | 211 |
| 5.2 | **ዓለም አቀፍ እውቅና የተገኘባቸው የአለካክ መስኮች/ወሰን ማስቀጠል ( ክብደት = 2.57 )** | | | | | | | | |
| 5.2.1 | 5 (በግዝፈት፣ በኤሌክትሪካል፣ በሙቀት፣ በይዘት እና ሚዛን) ዓለም አቀፍ እውቅና የተገኘባቸው የአለካክ መስኮች ማስቀጠል | 0.83 | በቁጥር | 5 | 5 | 5 | | | |

3. የ2015 በጀት ዓመት ዒላማዎችና የድርጊት መርሃ ግብር የተከለሰ

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | የ2014 አፈፃፀም (መነሻ) | የ2015 ግብ (ዓመታዊ) | ሩብ ዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| 5.2.2 | ዕዉቅና ባልተገኘባቸው 6 የአለካክ መስኮች (በዳይሜንሽናል፣ በሀይል፣ ይዘት (ላርጅ ቮልዩም) ፣ በቶርክ፣ በሀርድነስ፣ በጊዜና ድግግሞሽ) የአለካክ መስኮች በተዘጋጀው ፕሮግራም መሰረት ዓመታዊ የውስጥ የጥራት ኦዲት በማከናወን የእርምት እርምጃ መውሰድ | 0.83 | በቁጥር | 4 | 6 | 6 | | | |
| 5.2.3 | አዳዲስ የንጽጽር ፕሮግራሞችን በግዝፈት፣ በግፊት እና በሚዛን የአለካክ መስኮች ማፈላለግ እና ማካሄድ | 0.90 | በቁጥር | 3 | 3 | | | 3 | |
| 5.3 | **በአዳዲስ የአለካክ መስኮች/ወሰን እውቅናን ማስፋት ( ክብደት = 2.5 )** | | | | | | | | |
| 5.3.1 | በ2 የአለካክ መስኮች በወበቅ (Humidity) እና በእርጥበት (Mositure) መስክ የካሊብሬሽን የአሰራር ስርዓት ሰነድ ማዘጋጀት እና ዕውቅና ማስፋት | 2.5 | በቁጥር | 0 | 2 | | | 1 | 2 |
| 5.4 | **በ3 አለካክ መስኮች በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት (BIPM-KCDB)ማስመዝገብ ( ክብደት = 1 )** | | | | | | | | |
| 5.4.1 | ኤሌክትሪካል፣ ሙቀት እና ይዘት የአለካክ መስኮችን በዓለም አቀፍ የሥነ-ልክ ድርጅት መረጃ ቋት /BIPM-KCDB/ የካሊብሬሽን ልኬት ብቃት/CMC/ ለማስመዝገብ የጥራት ሥራ አመራር አሰራር ሥርዓት ሰነድ በክፍለ አህጉራዊ የሥነ-ልክ ድርጅት የጥራት ቴክኒካል ኮሚቴ /AFRIMETS TC-QS/ ማስገምገም | 1 | በቁጥር | 0 | 1 | | | | 1 |
| 5.5 | **በአህጉራዊና ዓለምአቀፍ የሥነልክ ተቋማት በመሳተፍ ስትራቴጂያዊ ተጠቃሚነትን ማሳደግ ( ክብደት = 1 )** | | | | | | | | |
| 5.5.1 | ከዓለምአቀፍ (BIPM) ከአህጉራዊ AFRIMET እና NEWMET ዓመታዊ ስብሰባ ላይ አገሪቷን ወክሎ መሳተፍ | 0.5 | በቁጥር | 1 | 1 | | 1 | | |
| 5.5.2 | ከአህጉራዊ AFRIMET እና NEWMET ዓመታዊ የቴክኒካል ስብሰባዎች ላይ መሳተፍ እና የንጽጽር ፕሮግራሞችን ማመቻቸት | 0.5 | በቁጥር | 0 | 2 | 1 | | | 2 |

3. የ2015 በጀት ዓመት ዒላማዎችና የድርጊት መርሃ ግብር የተከለሰ

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደ ት | መለኪያ | የ2014 አፈፃፀ ም (መነሻ) | የ2015 ግብ (ዓመታ ዊ) | ሩብ ዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| 5.6 | **የጥራት ስራ አመራር ስርዓቶችን በመለየት ተግባራዊ ማድረግ ( ክብደት = 1.5 )** | | | | | | | | |
| 5.6.1 | በ 4 የስራ ሂደቶች (በሳ/መ/ስ/ም/ዳ/ት፣ በሳ/መ/ቴ/ም/ዳ/ት ፣በፋይናንስ ዳ/ት ፣ሰው ኃብት አስ. ዳ/ት (ISO 9001:2015) ተግባራዊ ማድረግ | 1 | በቁጥር | 0 | 1 | | | | 1 |
| 5.6.2 | የሳይንስ መሳሪያዎች ፍኖተ ካርታ ማዘጋጀት | 0.5 | በቁጥር | 0 | 1 | | | | 1 |
| 6 | **የአለካክ ወሰኖችን ማሳደግ ( ክብደት = 4 )** | | | | | | | | |
| 6.1 | **የአለካክ መስክ/ወሰን ማሳደግ ( ክብደት = 4 )** | | | | | | | | |
| 6.1.1 | አራት(4) የአለካክ መስኮች/ወሰኖች ማሳደግ | 4 | በቁጥር | 0 | 4 | | | 2 | 4 |
| 7 | **የአሰራር ቅልጥፍናን ማሻሻል ( ክብደት = 1 )** | | | | | | | | |
| 7.1 | **የተሻሻሉና አዳዲስ ኦላይን ሲስተሞች ተግባራዊ ማድረግ ( ክብደት = 1 )** | | | | | | | | |
| 7.1.1 | በተቋሙ ጥቅም ላይ እየዋሉ ያሉትን ሲስተሞችን (IFMIS, ICMIS፣EGPS) አጠናክሮ ለማስቀጠል ክትትል እና ድጋፍ ማድረግ | 0.2 | በቁጥር | 2 | 3 | 1 | 2 | 3 | |
| 7.1.2 | የካሊብሬሽን እና የጥገና አልግሎት (አውቶሜት) E-service አላይን በማድረግ የአገልግሎት አሰጣጡን ማዘመን | 0.8 | በቁጥር | 0 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 7.2 | **ደንቦች፣ መመሪያዎችና ውሎች ማዘጋጀትና መከለስ ( ክብደት = 0.4 )** | | | | | | | | |
| 7.2.1 | የአገልግሎት ክፍያ የዋጋ ተመን ሰነድ መከለስ እና ለገ/ሚ ማቅረብ | 0.3 | በቁጥር | 0 | 1 | | | 1 | |
| 7.2.2 | የሚጸድቁ ረቂቅ የህግ ማእቀፎችን ሂደት መከታተል | 0.1 | በቁጥር | 2 | 2 | | 2 | | |
| 7.3 | **የጥናት ምርምር እና መመሪያ ማዘጋጀት ( ክብደት = 0.5 )** | | | | | | | | |

3. የ2015 በጀት ዓመት ዒላማዎችና የድርጊት መርሃ ግብር የተከለሰ

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | የ2014 አፈፃፀም (መነሻ) | የ2015 ግብ (ዓመታዊ) | ሩብ ዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| 7.3.1 | የጥናት እና ምርምር መመሪያ ማጸደቅ ተግባራዊ ማድረግ | 0.5 | በቁጥር | 0 | 1 | | | | 1 |
| 7.4 | **የአገልግሎት ፣የመሳሪያ ግዢ እና የአባልነት ክፍያ መፈጸም ( ክብደት = 1 )** | | | | | | | | |
| 7.4.1 | በግዥ ዕቅዱ መሠረት የሀገር ውስጥ እና የውጪ ግዥ በመፈፀም ማጠናቀቅ | 1 | በመቶኛ | 2 | 2 | | | 1 | 2 |
| 7.5 | **የንብረት ቆጠራ ማካሄድ እና ስራ ላይ የማይውሉ ንብረቶችን በወቅቱ ማስወገድ ( ክብደት = 1.5 )** | | | | | | | | |
| 7.5.1 | በዓመታዊ ንብረት ቆጠራ ውጤት መሠረት ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ንብረቶችን በየዓይነታቸው መለየት እና በአስወጋጅ ኮሚቴ እንዲወገዱ ማድረግ | 0.7 | በቁጥር | 1 | 1 | | | 1 | |
| 8 | **ቅንጅታዊ አሰራር ማሻሻል ( ክብደት = 2.5)** | | | | | | | | |
| 8.1 | **ከከፍተኛ ትምህርትና የምርምር ተቋማት ጋር በትብብር መስራት( ክብደት = 1 )** | | | | | | | | |
| 8.1.1 | ከተለያዩ ዩኒቨርስቲዎች ለሚመጡ 21 ተማሪዎች ኢንተርንሺፕ ፕሮግራም ማካሄድ | 1 | በቁጥር | 18 | 21 | | | 14 | 21 |
| 8.2 | **ከአቻ የውጪ የሥነ-ልክ ተቋማት ጋር በትብብር መስራት ( ክብደት = 1 )** | | | | | | | | |
| 8.2.1 | ከ5 ከአቻ የውጪ የሥነ-ልክ ተቋማት ጋር የተፈረመውን ስምምነት ማደስ እና ተግባራዊነቱን መከታተል | 1 | በቁጥር | 3 | 5 | | 2 | | 5 |
| 8.3 | **ከጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ጋር በትብብር መስራት ( ክብደት = 0.5 )** | | | | | | | | |
| 8.3.1 | ከጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት ጋር በትብብር መስራት | 0.5 | በቁጥር | 2 | 2 | | 1 | | 2 |
| 9 | **የሰራተኛውን ብቃት ማሳደግ ( ክብደት = 8 )** | | | | | | | | |
| 9.1 | የሰው ሀብት ልማት ማልማት | 3 | | | | | | | |

3. የ2015 በጀት ዓመት ዒላማዎችና የድርጊት መርሃ ግብር የተከለሰ

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደ ት | መለኪያ | የ2014 አፈፃፀ ም (መነሻ) | የ2015 ግብ (ዓመታ ዊ) | ሩብ ዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| 9.1.1 | ለሠራተኞች ስልጠና መስጠት | 1 | በቁጥር | 150 | 180 | 40 | 115 | 180 | |
| 9.1.2 | ሁለተኛ እና ሶስተኛ ዲግሪ የትምህርት ዕድል መስጠት | 0.5 | በቁጥር | 6 | 3 | 2 | 3 | | |
| 9.2 | **የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ ስልቶችን መቀየስ፣፣ መከታተልና ማጠናከር ( ክብደት = 2.5)** | | | | | | | | |
| 9.2.1 | ኤች አይቪ በደማቸዉ ዉስጥ ለሚገኝ ሁለት የኢንስቲትዩቱ ሠራተኞችና ወላጆቻቸዉን ላጡ ሁለት ሕፃናት ድጋፍ ማድረግ | 0.5 | በቁጥር | 20964 | 21600 | 5400 | 10800 | 16200 | 21600 |
| 9.2.2 | ዝቅተኛ የደሞዝ ተከፋይ የሆኑ ሴቶችና ወጣት ሠራተኞችን ፕሮጀክት በመንደፍ ገቢያቸዉን እንዲያሳድጉ ማመቻቸት | 2 | በመቶኛ | | | | 100 | | |
| 9.3 | **የተቀናጀ የሙስናና የመከላከል ስትራቴጂ ተግባራዊ ማድረግ ( ክብደት = 2.5)** | | | | | | | | |
| 9.3.1 | በተቋም የሚገኙ የስራ ክፍሎችን የሙስና ተጋላጭነት ስጋት መለየት፣ ደረጃ መስጠት ፣ለተቋሙ ይፋ ማድረግ እና መከታተል | 0.3 | በመቶኛ | 100 | 100 | | 100 | | |
| 9.3.2 | በተቋም ለሙስና ተጋላጭነት ስጋት በሆኑ አሰራሮች ላይ የአሰራር ሥርዓት ጥናት ማካሄድ | 0.4 | በመቶኛ | 0 | 1 | | | | 1 |
| 10 | **የስራ አካባቢና መሰረተ ልማት ማሻሻል ( ክብደት = 11)** | | | | | | | | |
| 10.1 | **የአካባቢ ብክለትንና በህብረተሰቡ ጤና ጉዳት መቀነስ ( ክብደት = 2)** | | | | | | | | |
| 10.1.1 | የሁለተኛ ምድብ የጨረራ ላቦራቶር /SSDL/ የ X-ray machine እና የ Cs-137 Gamma source shutter ብልሽት ተከታትሎ በማስጠገን እንደገና አገልግሎት ማስጀመር | 1 | በቁጥር | 0 | 2 | | | 2 | |
| 10.2 | **ተስማሚ የሆኑ የሥራ ቦታዎች ማዘጋጀት ( ክብደት = 2)** | | | | | | | | |

3. የ2015 በጀት ዓመት ዒላማዎችና የድርጊት መርሃ ግብር የተከለሰ

| ተ.ቁ | ስትራቴጂክ ግቦች፣ ዋና ዋና ተግባራት እና ዝርዝር ቁልፍ የአፈፃፀም አመልካቾች | ክብደት | መለኪያ | የ2014 አፈፃፀም (መነሻ) | የ2015 ግብ (ዓመታዊ) | ሩብ ዓመት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | 1ኛ | 2ኛ | 3ኛ | 4ኛ |
| 10.2.1 | ተስማሚ የሆኑ የሥራ ቦታዎች ማዘጋጀት (ግቢ ውበት፣ፋሲሊቲ ፣ እድሳት እና የሰራተኛ መመገቢያ) | 2 | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 10.3 | **የሰው ኃይል ማሟላት ( ክብደት = 3)** | | | | | | | | |
| 10.3.1 | በፀደቀው መዋቅር መሰረት ድልድል ማካሄድ | 3 | በመቶኛ | 0 | 100 | | | | 100 |
| 10.4 | **የኢ/ኮ/ቴ መሠረተ ልማት ደህንነትና ወቅታዊነት ማስጠበቅ ( ክብደት = 2)** | | | | | | | | |
| 10.4.1 | በተቋሙ የሚገኙ መሠረተ ልማቶችን (ሀርድዌር እና ሶፍት ዌር) አቅም መጨመር | 1 | በቁጥር | 0 | 1 | | | 1 | |
| 10.5 | **የለውጥና መልካም አስተዳደር የአሰራር ስርዓቶች መዘርጋት ( ክብደት = 2)** | | | | | | | | |
| 10.5.1 | በዜጎች ቻርተር መሠረት አገልግሎት መስጠቱን የትንተና ሰነድ ማዘጋጀት | 0.33 | በቁጥር | 1 | 2 | | | | 2 |
| 11 | **የክትትልና የግምገማ ስርዓትን ማሻሻል ( ክብደት = 3)** | | | | | | | | |
| 11.1 | **ፕሮጀክቶችን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ( ክብደት = 1)** | | | | | | | | |
| 11.1.1 | ፕሮጀክቶችን በየሩብ ዓመቱ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ | 1 | በቁጥር | 4 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 11.2 | **የውጤት ተኮር ዕቅድ ማዘጋጀትና አፈጻጸም መገምገም ( ክብደት = 2)** | | | | | | | | |
| 11.2.1 | የውጤት ተኮር ዕቅድ ማዘጋጀት፣ በየደረጃው መፈራረም ፣ በየወሩ አፈጻጸም መገምገም እና ምዘና ማካሄድ | 2 | በቁጥር | 3 | 3 | 2 | | 3 | |

## 4. የዓመቱን ዕቅድ ለማሳካት የሚተገበሩ ማስፈጸሚያዎች

### 4.1 የማስፈጸሚያ ስትራቴጂዎች

- የተዘጋጀውን አደረጃጀት ማጸደቅ እና ምደባ ማከናወን
- ዕውቀት ክህሎትና ሥነምግባር የተላበሰ የሰው ኃይል መገንባት፣
- የውጤት ተኮር ምዘና ስርዓትን በቀጣይነት ተግባራዊ ማድረግ፤
- ከኢንዱስትሪዎች፤ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፤ ምርምርና ስልጠና ተቋማት፤እና ህግ አስፈጻሚ አካላት ጋር በቅንጅት መስራት፤
- ከብሔራዊ፤ አህጉራዊና አለም አቀፍ ተቋማት ጋር ያሉ ትብብሮችን መጠቀም፤
- ምርጥ ተሞክሮ በመቀመር የአሰራር ሥርዓትን በማሻሻል፣
- በሥነ-ልክ እና የሳይንስ መሳሪያዎች ተግባራት ዙሪያ ለህብረተሰቡ ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ በመስጠት፤
- ከተለያዩ ተቋማት የሚደረጉ የመግባቢያ ስምምነቶችን ወደ ፕሮጀክት መለወጥና ተጠቃሚነትን በማስፋት
- የብልሹ አሰራርና አመለካከትን በመቀየር መልካም አስተዳደርና ሥነ-ምግባርን ማስፈን
- በሴክተር ዘለል ተግባራትና  የአካባቢ ጥበቃ ጉዳዮችን አካትቶ በመስራት፤

### 4.2 ተቋማዊ የትራንስፎርሜሽን እና የኢኮቴ ዲጂታላይዜሽን አጀንዳዎች

ኢንስቲትዩቱ በደንብ የተሰጠውን ኃላፊነት እና ተግባር በአግባቡ ለመወጣትና በቀጣይ የታቀዱትን ተግባራት ለመፈጸም የሚያስችል አደረጃጀት ተጠንቶ ለማጸደቅ በክትትል ሂደት ላይ ነው፡፡ በተጨማሪም የኢንስቲትዩቱ ማቋቋሚያ ደንብ ጸድቆ ስራ ላይ ከዋለ አስራ አንድ ዓመታትን ያስቆጠረና በአፈጻጸም፣ በአደረጃጀት፣ በተጠሪነት እና በመሰረታዊ ስልጣንና ተግባር ረገድ ውስንነቶች ያሉበት በመሆኑና ይህንንም በመቅረፍ በዘርፉ የሃገሪቱ ፍላጎት አሁን ከተደረሰበት ደረጃ ጋር ማጣጣም በማስፈለጉ እና ለሃገራዊ ልማት የሚያበረክተውን ሚና በብቃት ለመወጣት የካሊብሬሽንና የዕርከን ተዋረድ ትስስር እንዲሁም የጥገና አገልግሎቶች በተጨማሪ በሥነ-ልክና በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፎች የተደረሰበትን የሳይንስና ቴክኖሎጂ እድገት ደረጃ በመከተል በዘርፉ የጥናትና ምርምር ተግባራት፣ የማማከር እና የስልጠና ስራዎችን ትኩረት አድርጎ እንዲሰራ ዓላማው ይህንን እንዲያካትት ተደርጎ ነባሩ ደንብ የተሻሻለ በመሆኑ ለማጸደቅ በክትትል ነው፡፡ የኢኮቴ እና ዲጂታላዜሽን በተመለከተ የካሊብሬሽን እና የጥገና አልግሎት (አውቶሜት) E- service ኦላይን ለማድረግ አገልግሎት አሰጣጡን ለማዘመን በጥራት መሰረተ ልማት ፕሮጀክት ጋር በመተባበር እየተሰራ ይገኛል፡፡ በተቋሙ የሚገኙ መሠረተ ልማቶችን (ሀርድዌር እና ሶፍት ዌር) አቅም በመጨመር  የኢኮቴ ስራውን ለማሳለጥ እየተሰራ ሲሆን በኢንስቲትዩቱ  ጥቅም ላይ እየዋሉ ያሉትን ሲስተሞችን (IFMIS, ICMIS፣e-GP) አጠናክሮ ለማስቀጠል የክትትል እና ድጋፍ ሥራው በዚህ በጀት ዓመት ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

## 4.3 የክትትልና ግምገማ ስርዓት

ኢንስቲትዩቱ የተቋቋመበትን ዓላማ ለማሳካት ወይም የተሰጡትን ተግባራትና ኃላፊነቶች በአግባቡና በተደረጀ መልኩ መወጣት የሚችለው አስተማማኝ የሆነ የክትትልና ግምገማ ስርዓት ሲኖረው ነው፡፡ ከዚሁ አንጻር ማንኛውም ተግባር ውጤታማ እንዲሆን ወቅታዊ ክትትልና ግምገማ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በዕቅድ ላይ የሰፈሩት ግቦች በተያዘላቸው የሥራ መርሀ-ግብር መሰረት ተገቢውን ግብዓቶች ማግኘታቸውን፣ በመመሪያዎችና ደንቦች መሰራታቸውንና ከታለመለት ዓላማ አንፃር ውጤት ማስገኘቱን ለመመልከትና ለመፈተሽ የሚያስችል የክትትልና ግምገማ ሥርዓት መዘርጋት ተገቢ ይሆናል፡፡

የክትትል ሥርዓት የማያቋርጥ በተከታታይነት የሚከናወን ተግባር ሲሆን በዋናነት የሥራ አፈፃፀሙ በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ፣ ለዚሁ ተግባር የዋለውን ሀብት አጠቃቀም፣ የተፈለገው ውጤት ላይ ለመድረስ እንቅፋት የሆኑ ጉዳዮችን በመለየት ለሚመለከተው አካል ወቅታዊ መረጃ ለመስጠት ያገለግላል፡፡ በመሆኑም ኢንስቲትዩቱ እየሰራባቸው ያሉ የክትትል ሥርዓቶችን በማዳበርና አዳዲሶችን በመዘርጋት በ2015 በጀት ዓመት የተከለሰውን ዕቅድ አፈፃፀም ውጤታማ ለማድረግ አቅዷል፡፡ በዚህም መሰረት የክትትልና ግምገማ ስርዓቱ ሶስት መስተጋብሮች ያሉት ሲሆን እነርሱም፡-

### 4.3.1 ሪፖርት

- እያንዳንዱ ፈጻሚ ሳምንታዊ ዕቅድና ሪፖርት ለቡድን መሪ ያቀርባል፡፡ የቡድን መሪው ከሪፖርቱ በመነሳት ለእያንዳንዱ ፈጻሚ ግብረመልስ ይሰጣል፡፡
- እያንዳንዱ ቡድን መሪ ሳምንታዊ ዕቅድና ሪፖርት ለስራ ሂደት መሪ ያቀርባል፡፡ የስራ ሂደት መሪው ከሪፖርቱ በመነሳት ለእያንዳንዱ ቡድን መሪ ግብረመልስ ይሰጣል፡፡
- እያንዳንዱ የስራ ሂደት መሪ ሳምንታዊ ዕቅድና ሪፖርት ለተቋሙ መሪ ያቀርባል፡፡ የተቋሙ መሪ ከሪፖርቱ በመነሳት ለእያንዳንዱ ስራ ሂደት መሪ ግብረመልስ ይሰጣል፡፡

### 4.3.2 የአካል ግምገማ

- የለውጥ ሰራዊት ቡድኖች በየሳምንቱ በአካል እየተገናኙ በሚቀርቡ ሳምንታዊ ዕቅድና ሪፖርት መሰረት ስራቸውን ይገመግማሉ፡፡ የቡድን መሪው ለእያንዳንዱ ፈጻሚ ግብረመልስ ይሰጣል፡፡
- በስራ ሂደት ፎረም ደረጃ በየሳምንቱ ሁሉም ፈጻሚዎች በተሳተፉበት የስራ ሂደቱ አፈጻጸም ይገመገማል፡፡ የስራ ሂደት መሪው ለሁሉም ቡድን መሪዎች ግብረመልስ ይሰጣል
- በተቋም ደረጃ በየሁለት ሳምንቱ ሁሉም የማኔጅመንት አባላት በተሳተፉበት የተቋሙ አፈጻጸም ይገመገማል፡፡ የተቋሙ መሪ ለሁሉም የማኔጅመንት አባላት የጹሁፍ ግብረመልስ ይሰጣል፡፡

- በጥራት መሰረተ ልማት ተቋማት በዘርፍ ደረጃ በየሩብ ዓመቱ ሁሉም የተቋሙ መሪዎች ባሉበት የየተቋማቱ አፈጻጸም ይገመገማል፡፡ ሚኒስትሩም ለሁሉም የተቋሙ መሪዎች ግብረ መልስ ይሰጣል፡፡

### 4.3.3 ሱፐርቪዥን

- የተቋሙ የሱፐር ቪዥን ኮሚቴ በየወሩ አንድ ጊዜ የለውጥ ስራውን በየስራ ሂደቱ በአካል በመገኘትና በመገምገም ድጋፍ ያደርጋል፡፡

## 5. ዕቅዱን ለማሳካት በየምዕራፍ የሚሰሩ ስራዎች

### 5.1 የዝግጅት ምዕራፍ (ሐምሌ-ነሀሴ)

- ዕቅዱን ከፈጻሚ ጋር የጋራ ማድረግ፤
- ዕቅዱን ለየስራ ሂደቱና በእያንዳንዱ ፈፃሚ ድርሻ መዘርዘር፤
- በየደረጃው የመፈራረም ስርአት ማካሄድ፤
- ተግባሩን ለመፈጸም መሰናክል የሚሆኑ ግብአቶችን በመለየት ግዥ ማከናወን፤
- ተገቢውን የክህሎት ስልጠና መስጠት

### 5.2 የተግባር ምዕራፍ (መስከረም-ግንቦት 20)

- በጸረ-ኪራይ ሰብሳቢነት ትግል እና መልካም አስተዳደርን በማስፈን ተግባራትን መፈጸም፤
- ጠንካራና የደከሙ አፈፃፀሞች በመለየት፤ የደከሙትን ለማጠናከር የሚያስችል ድጋፍ ይደረጋል፤
- የሪፖርትና የግምገማ ስርዓቶች በትክክል በማከናወን ጥቅም ላይ ማዋል፤5

### 5.3 የማጠቃለያ ምዕራፍ (ግንቦት 21 -ሰኔ 30)

- በዕቅዱ የተያዙ ግቦች መሳካት አለመሳካታቸውን በቢኤስሲ አግባብ መመዘን፤
- ስኬትና ውድቀትን ከማምጣት አኳይ በዝግጅትና በተግባር ምዕራፍ አፈፃፀም ላይ የነበሩ ድክመቶችና ጥንካሬዎች መለየት፤
- ከአሉታዊም ሆነ ከአወንታዊ የተግባራት አፈፃፀም ሊወሰዱ የሚችሉ ትምህርቶች በጠራ ሁኔታ ተለይተው ለቀጣዩ ግብዓት ሆነው እንዲያገለግሉ ይደረጋል፤
- እያንዳንዱ ባለድርሻ አካል ከተሰጠው ተልዕኮ አኳያ ያደረገውን እንቅስቃሴ በጥልቀትና በተጨባጭ አካሄድ ይመዘናል፤
- በአስፈፃሚ አካላት መካከል ግምገማ ይካሄዳል፣ ሂደቱም የመገነባቢያ መድረክ እንዲሆን ከኪራይ ሰብሳቢነት በፀዳ ሁኔታ ይከናወናል፤

6. የ2015 በጀት ዓመት የሰው ሃይል ፍላጎት

| የልማት ፕላን የሰው ኃይል ፍላጐት በትምህርት ደረጃ/በሙያ መስክ | |
|---|---|
| | መነሻዓመት (Stock) |
| ኮሌጅ ዲፕሎማ | |
| በተፈጥሮ | |
| በማበራዊ | 2 |
| የመጀመሪያ ዲግሪ | |
| በተፈጥሮ (BSC) የሙያ መስክ | |
| ኬሚስትሪ/ፊዚክስ | |
| በምህንድስና ሳይንስ ኢንጂነሪንግ | 3 |
| በማህበረሰብ ሳይንስ ሙያ መስክ | |
| ማኔጅመንት | 3 |
| ኢኮኖሚክስ | |
| የሂሳብ አያያዝ | 2 |
| ሁለተኛ ዲግሪ | |
| በተፈጥሮ (BSC) የሙያ መስክ | |
| ሦስተኛ ዲግሪ | |
| በተፈጥሮ (BSC) የሙያ መስክ | |
| ድምር | 10 |

## 7. 2015 በጀት ዓመት የፊዚካል እና የፋይናንስ ዕቅድ በየውጤቱ (የጸደቀ በጀት)

| የፕሮግራም ስም/ የፕሮግራም ውጤት መግለጫ | የውጤት መለኪያ | 2015 በጀት ዓመት የፊዚካል እቅድ | | | | 2015 ዓመት የፋይናንስ ዕቅድ /በሚሊዮን ብር / | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
| **ፕሮግራም 1፡ የሥራ አመራርና ድጋፍ አገልግሎት** | | | | | | | | | |
| ውጤቶች | | | | | | | | | |
| ውጤት 1፡ የተሰጡ የድጋፍ አገልግሎቶች | በ% | 20 | 30 | 30 | 20 | 7.87 | 6.86 | 4.20 | 4.20 |
| **ፕሮግራም 2፡ የኢትዮጵያ የሥነ-ልክ ስርዓት ዝርጋታና ድጋፍ** | | | | | | | | | |
| ውጤቶች | | | | | | | | | |
| ውጤት 1፡ ያደጉ የአለካክ ወሰኖች | በቁጥር | | 2 | 1 | 1 | 0.96 | 0.87 | 0.72 | 0.72 |
| ውጤት 2፡ ዓለም አቀፍ ዕርከን ተዋረድ የጠበቁ ብሔራዊ ማነጻጸሪያዎች | በቁጥር | 48 | 57 | 61 | 45 | 0.19 | 1.23 | 0.85 | 0.12 |
| **ፕሮግራም 3፡ ካሊብሬሽንና የልኬት** | | | | | | | | | |

| የፕሮግራም ስም/<br><br>የፕሮግራም ውጤት መግለጫ | የውጤት መለኪያ | 2015 በጀት ዓመት የፊዚካል እቅድ | | | | 2015 ዓመት የፋይናንስ ዕቅድ /በሚሊዮን ብር / | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት | 1ኛ ሩብ ዓመት | 2ኛ ሩብ ዓመት | 3ኛ ሩብ ዓመት | 4ኛ ሩብ ዓመት |
| ውጤቶች | | | | | | | | | |
| ውጤት 1፡ የተሰጡ የካሊብሬሽን አገልግሎቶች | በቁጥር | 6750 | 8187 | 8187 | 7941 | 4.09 | 4.81 | 1.78 | 0.69 |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ፕሮግራም 4፡ የሳይንስ መሳሪያዎች አቅም ግንባት** | | | | | | | | | |
| ውጤቶች | | | | | | 0.92 | 1.39 | 1.32 | 0.15 |
| ውጤት 1፡ በሳይንስ መሳሪያዎች ዘርፍ የተሰጡ የማማከር አገልግሎቶች | በቁጥር | 1 | 1 | 1 | 1 | 0.92 | 1.39 | 1.32 | 0.15 |
| ውጤት 2፡ የተሰጡ የብቃት ማረጋገጫ አገልግሎት | በቁጥር | 5 | 7 | 8 | 6 | 0.04 | 0.055 | 0.04 | 0.04 |
| ውጤት 3፡ የተሰጡ የሳይንስ መሳሪያ የጥገና አገልግሎቶች | በቁጥር | 25 | 90 | 90 | 95 | 1.02 | 1.02 | 0.53 | 0.19 |
| ውጤት 4፡ የተሰጡ የምህንድስና አገልግሎቶች | በቁጥር | 3 | 12 | 10 | 5 | 0.22 | 0.38 | 0.11 | 0.04 |